# ወያኔ እንኳን “ሽፍታ” መባሉ “ጋኔልም” ሲያንሰው ነው!

ጌታቸው ረዳ መጋቢት 25/2004 ዓ.ም
(www.ethiopiansemay.blogspot.com)

መልስ ለጋዜጠኛ ዮናስ በላይ አበበ (መቀሌ)

ከስር የሚታየው ፎቶግራፍ የወያኔ ታጋይ በነበረበት ወቅት መርማሪ ሹም ሆኖ እስረኞችን በእሳት ሲጠብሱ እና ሲያሰቃዩ ከነበሩት ወያኔ ሥልጧን ከተቆጣአጠረ ወዲያ ያየር ሃይል ዋና አዛዠኸ የነበረው ብ/ጀኔራል አበበ ተክለሃይማኖት ነው።

EthioLion.Com



EthioLion.com



ይህ ጽሑፍ ለአቡጊዳ ድረገጽ የተላከ ነበር። በተለያዩ የራሳቸው ምክንያት ድንገት ካላወጡት በሚል ወደ ሌሎች ድረገጾች ተልኳል። ከዚህ በተጨማሪም የድረገጻቸው ግላዊ ኢመይል ለማግኘት በጣም አስቸጋሪ ስለሆነ መላክ አልተቻለም። መልእክት ሳጥናቸው ብገባም ሕዝባዊ የትችት መስጫ ሳጥን በመሆኑ በፒዲኤፍ ለመላክ አስቸጋሪ ነውና፤ ይህንን አንብበው ወደ እኔ ከጻፉልኝ እልክላቸዋለሁ፡ ካልሆነ ግን ይሄው በሌሎች ድረገፆች ተሰራጭቷል አንብቡት።

አቡጊዳዎች መጀመሪያ ሰላም እላለሁ። አቡጊዳዎች ይህ እንደምትለጥፉት ተስፋ አደርጋለሁ። ጸሃፊው ጋዜጠኛ ዮናስ በላይ አበበ (ከመቀሌ) "የመቀሌው ገረብ ቡቡ የአፓርታይድ መንደር" ብሎ "ፍትሕ" በሚባለው "ጋዜጣ" ስለጻፈው ዘገባ ጽሑፍ ከናንተው ገጽ ለሁለተኛ ጊዜ ማንበቤ ነው። አስፈላጊ መሆኑን አምናችሁ ለሁተኛ ጊዜ የለጠፋችሁት መሆኑን ስገነዘብ ትኩረቱ ከባድ መሆኑን ለማስገንዘብ ይመስለኛል ያተማችሁት።

ይህ ከሆነ፤ ጸሃፊው ጋዜጠኛ ዮናስ በላይ አበበ (ከመቀሌ) "የአፓርታይድ መንደር በመቀሌ" ብሎ "ፍትሕ" በሚባለው "ጋዜጣ" ስለጻፈው ዘገባ ጠቃሚ ቢሆንም፤ ጋዜጠኛው ወያኔዎችን በጥቅሉ ሽፍቶች አትበሏቸው፤ (ሂፕክሪት እንኳ ቢሆንም) ከሽፍታ ውጭ ባህሪ የነበራቸው ፍትሕ ሰጪዎችም ነበሯቸው

ሲል “ወያነ ትግራይ” ይህ ሁሉንም የቀላቀለ ባሕሪ የነበረው ምን ብለን እንድንጠራው ግን ሳይነግረን” በቅቤ አሻሽቶ ለማቅርብ የመሞከሩ ጉዳይ በትግሬ ጋዜጠኞች አዲስ ነገር አይደለም። በደርግም ሆነ የዘውዱ ስርዓትም እኮ “ቀማኛም ሆነ ለፍትህ ብለው ራሳቸውን ለጥይት የሰጡ ወይንም ለሞት የዳረጉ ፍትህ ሰጪዎች ነበሯቸው”። ስርዓትን እንደ መሪዎቹ ባሕሪ እና ስርአትን እንደ ስርዓት እንጂ “ከጥሬ አንድ ብስል ስለነበረው” እየለቀምን እንለየው ማለት ‘አለመብሰል ነው”። ለዚህ ለዚህማ ‘ሻዕቢያው ተስፋዬ ገብረብም በቅርቡ “መለስን ማን ይተካዋል” በሚለው ልበወለድ ጽሑፉም እና “የፈረደባት ኤርትራ” ብሎ ኢትዮጵያዊያን ስለ “ፈረደባት/ምስኪኗ ኤርትራ” እንዴት እንደሚወተውቷት ምሬቱ በገለጸበት ሃተታ ውስጥም ሆነ በሌሎቹ ጽሑፎቹም እኮ ድርጅቱ አንዳንድ የዋሆችና ከሽፍታ ባሕሪ ውጭ የነበሩ ሰዎች እንዷሏቸው ጠቅሷል።ይሄ ግን ወያኔን ከሽፍታነት ባሕሪነቱ ነፃ አያወጣውም።

በተለይ ይህ የፍትሕ ጸሐፊ ወጣት እንደተቀሩት በወያነ ትግራይ ዘመን ያደገ ስለሆነ እኩያዎቹ ሁሉ በድርጅቱ ላይ ብዙ ጨከን አይልም።ለዚህም አብዛኛዎቹ ከቡድን 1 ወያኔ (መለስ) ወጥተው ወደ ቡድን 2 ወያኔ (ዓረና) የተሸጋገሩ ወጣቶችና ጋዜጠኞች (ወይንም መለስን የሚቃወሙ ጻሀፊዎች) “ገብሩ አስራትን እና አረጋሽ እንዲሁም አውዓሎምን “ከሽፍቶቹ” የተለዩ “ዲሞክራቶች ወይንም ከሃብት ምዝበራ ነፃ የሆኑ ድሃዎች” እያሉ ማቆነጃጀት አዲስ አይደለም። ስለሆነም፤ እስኪ ጋዜጠኛው ዮናስ ከመቀሌ ምን እንዳለ እንመለከት።እንዲህ ይላል፡

*“ሽፍታ በህዝብ መካከል እንደሚገኝ ሁሉ በተወሰኑ ወያኔዎችም መካከል ሊገኝ እንደሚችል ነው፡፡ እነሱ ግን በደፈናው ..በሽፍታ.. ስም ሊጠሩ አይገባም። (ጸሐፊው እነሱ የሚላቸው ምሳሌ ሲሰጥ ደግሞ “እነ ገብሩ አስራትን ነው”።) በትግራይ ህዝብ ላይ የሚዘንበውን የጭቆና ዝናብ ለማስቆም በእውቀትም ሆነ በስሜት ወደ በርሃ የወጡት ..የቁርጥ ቀን.. ወገኖች፣ ..ወንበዴ.. እየተባሉ፣ በተቆጣጠሩት መሬት (ሓራ መሬት) ዋርካ እግር ስር ሆነው ይሰጡት የነበረ ፍትህ ግን የሽፍታ ሳይሆን የራስ ሚካኤልን ፈለግ የተከተለ እንደ ነበር ዛሬም የአይን ምስክሮች አሉ።*

*በዚህን ወቅት ከእነ ተወልደ ቡድን ነጥሎ አቶ መለስ ያነጋገሩት ሌላው ሰው ደግሞ፤ ገብሩ አስራት ይባላል፡፡ መለስ ገብሩን ወደ እራሳቸው ቡድን ለመመለስ አበክረው ስለፈለጉ ..ገብሩ ተው.. እነሱ የያዙትን ይዘዋል አንተ ግን ትጎዳለህ፡፡ ማሃረምህን አንጥፈህ ነው ወደ መለመን የምትገባው..? አሉና በነባሩ ማስፈራሪያቸው የገብሩን አቋም ተፈታተኑት፤መለስ ዜናዊ፡፡ ..ታጋይ እኮ ነኝ.... ሲልም ገብሩ መለሰ፡፡ ይህ ብዙ ትርጉም አለው፡፡ ለህዝብ የታገለ፣ በህዝብ ድጋፍ እዚህ የደረሰ ህዝብ ያኖረዋል፡፡ እኔ ወያኔ እንጂ ሽፍታ አይደለሁም ማለቱ ነበር፡፡ አቶ ገብሩ፡፡ እንደነዚህ አይነት ወያኔዎቸም አሉ፡፡ እነዚህ ከወጡ*

EthioLion.Com

*በኋላ ነገረ ስራቸውን አወቅን እንጂ ስንት ምርጥ የህዝብ ልጆች በድርጅቱ ውስጥ እንዳሉ አምናለሁና፤ እንክርዳዱን ከስንዴው መለየት ተገቢ ይመስለኛል፡ ፡"*

ሲል እነ ገብሩን "ምርጥ የሕዝብ ልጆች" ናቸውና "ሽፍቶች" አትበሏቸው ሲል አቆነጃጅቶ ያቀርባቸዋል። ለምርጥነታቸው፤ መረጃ የሰጠን ደግሞ "መለስ ዜናዊ፡ በገብሩ ስለተናገረው "ምስክርነት" ነው።የአይጥ ምስክሯ ድምቢጥ"።

EthioLion.Com

"ይድረስ ለጎጠኛው መምህር "ወይንም "የወያኔ ገበና መህደር" (ደራሲ ጌታቸው ረዳ) በገጽ 302 የትግራይ ዲያቆናትና የቀሳውስት እምባ" ጋዜጠኛ ዮናስ አፈላልጎ እንዲያነበው እየጋበዝኩት፡በዚህ ታሪክ ፡በወየኔ እጅ የተሰቃዩ የትግራይ አዛውንቶች እና ወጣቶች ወያኔዎችን "ሽፍቶች" ወይንም "ትግራይን ለመቅጣት ከገሃነም የወረዱ" ብሎ ለምን እንደሚላቸው ምሳሌ ልስጥ።

በተለይ "ዲሞክራት" ነበር የሚለን የፈዳይን(ነብሰ ገዳይ ቡድን) ሃላፊ እና ፈራሚ ከነበሩት፤ ብዙ ነብሳት በእነሱ የስልጣን ትእዛዝ እንዲሰወሩ ካደረጉት አንደኛው ፤ብዙ ዘግናኝ ድርጊቶች ሲፈጸሙ የሚያወቅ፤ ገብሩ አስራት፤ "ልጆቻችን ስትገድሉ እና ስታስገድሉ ያለ ፍትሕ ስለነበር "ልዩ ፍረድ ቤት ተቋቁሞ ወያኔዎችን የምንፋረድበት ፍትሕ ይቋቋም" ብሎ እሮሮረ ላሰሙ የትግራይ እናቶች እና አባቶች ወንድሞችና እህቶችቻችን ገብሩ ምን ብሎ ነበር?



መረጃዎቹን ላቅርብ።

የ.ህ.ወ.ሐ.ት. ታጋዮች በሰባት ጥይት ደብድበው ሜካ ወስደው ጣሉኝ) ብሎ በወቅቱ የ35 አመት እድሜ የነበረው የዓድዋ ተወላጅ ብርሃነ ገብረህይወት የተባለ ዲያቆን "ወያኔዎች የተባሉ ዘመናዊ ሽፍቶች" ምን ግፍ እንዳደረሱበት በተጠቀሰው መጽሐፎ በሰፊው የተዘገበው አሳዛኙ ዘገባ ታበናላችሁ። ይህ የሰብአዊ እና የዜጎች መብት ጥሰት እሮሮ የወያኔ ጸሐፍትና ጋዜጠኞች እንዲሁም ካድሬዎቻቸው ድርጅታቸው የሰው ልጆች መብት አክባሪ፤ የመናገር፤ የመተቸት መብት በስፋት ለታጋዮቹም ሆነ ለትግራይ ሕዝብ አጐናጽፏል ሲሉ "ውሸት" እየነዙ ሐቁን የሆነውን ግን እየደበቁ የሕዝብ ተቆርቋሪነታቸው ምን ያህል

ጠማማ እንደነበረ ከበፊቱ ይልቅ ብዙ ትግል ካደረግን በኋላ ዛሬ ቀስ በቀስ ሕዝቡ እየተረዳው ሄዷል የሚል እምነት አለኝ።

ዛሬም በነፍጥ በተቆጣጠሩት ሚዲያቸውና የሕትመት ተቋማት ውሸታቸውን ቀጥለውበታል። የሚያሳዝነው ግን ትግራይ ውስጥ ነፃ ዘጋቢዎች ነን የሚሉ ወጣቶች ታጭቦ ጭቃ እየሆኑ ነው። በቅርቡ የትግርኛ ቪኦኤው ዘጋቢ “ግርማይ ገብሩ” የተባለው ጽ/ቤቱ መቀሌ ውስጥ ያደረገ ወጣት ጋዜጠኛ ‘ራዲዮ መርሃዊት” በተባለው ዋሺንግተን ዲሲ ውስጥ በትግርኛ ያስተላለፈው ከወያኔነት ጭቃ ያልወጣ ጽሑፍ ለመረመረው ሰው ‘ብዙ እርምጃ” እንደሚቀራቸው ታስተውሉታላችሁ። ወያኔ ባይኖር ደርግ የሚጥለው ፍጡር/ድርጅት አይኖርም ነበር ብሎ ያላቸው ማን ነው? ለመሆኑ ወያኔ ደርግ የተባለው አረመኔ ስርዓት ጥሎ ለኢትዮጵያ ያስከተለባት መዘዝ እና ጦርነት፤ ዘረኛነት፤ግጭት....አመጣልን ብለው እነዚህ የትግራይ ጋዜጠኞች ከሚለፍፉት ዝበዝንኬ ለውጥ ሚዛን ላይ ቢቀመጥ የትኛው ያመዝናል? የቪኦኤው ግርማይ ገብሩ እንደሚሞነጫጭረው ወያኔ “በሳሙና” ታጠበ አልታጠበ ወያኔ “ነጥቶ” ተጨምቆ ምንድነው ልናገኘው የምንችለው ንጣትና ጥራት?

እውነት ተሸፋፍኖ አይቀርምና ሰሚ አጥተው በየቤቱ በጸጥታ የተዋጡ የሚጮህላቸው ያጡ ዜጎች እሮሮአቸው ፍትሕ አጥቶ ለዓመታት የደም ዕምባ ያፈሰሱት የወያኔ ሰለባዎች የሆኑት የትግራይ ቀሳውስትና ዲያቆናት በወቅቱ የትግራይ ክፍለሀገር (የትግራይ ክልል መንግሥት ይሉታል በዛሬው በወያኔዎች አጠራር) የጋዜጠኛ ፍኖስ አበበ “ዓይኒ ማዓር” (ብርቅየ) “የፍትሕ ሰው/ዲሞክራት/አምስት ሳንቲም የሌለው ድሃ” “ታጋይ ገብሩ አስራት” ፕረዚዳንት በነበረበት ወቅት “በረሃ እያለን ለፈጸምነው ወንጀል አንጠየቅበትም” ብሎ በወያኔ የተጠቁ ፍትሕ ፈላጊዎች እሮሮረ ሲያቀርቡለት በሥልጣን ማን ያህለኝነት ያሰናበታቸው አቶ ገብሩ አስራት እና የእርሱ ረዳት የነበረቺው ወ/ሮ አረጋሽ አዳነም በጠቀስኩት መጽሐፌ የተዘገበው ታሪክ የተጠቀሱበትን ሁኔታ መመርመር ያስፈልጋል።

ዲያቆን ብርሃነ ገብረሂይወት ወደ ሕዝባዊ ወያነ ሐርነት ትግራይ (ሕወሓት) ትግል ውስጥ እንዲቀላቀል የቀረበለትን ጥሪ ባለመቀበሉና በመቃወሙ፤ በተደጋጋሚ መታሰሩንና በመጨረሻም በአሰቃቂ ሁኔታ በሰባት ጥይት መደብደቡን ታሪኩን አንብባችሁ ይሆናል። ይህ ወጣት ቤተክርስቲያን በማገልገሉም ሳቢያ፤ ከፍተኛ ተጽዕኖ ተደርጎበት የዲቁና መታወቂያውንም የሕወሐት ታጋዮች ቀዳድደውበታል። የደረሰበት ጉዳት ከፍተኛ በመሆኑ በሀገር ውስጥ ሕክምና የማይድን መሆኑንም የጥቁር አንበሳ ሆስፒታል (1986 ዓ.ም) አረጋግጧል።20 የሚሆኑ የወያኔ ሽፍቶች አንጀቱ እንደ ሜዳ ፍየል እያባረሩ በጥይት በሳስተውት “መግል ፤ደም እና ዓይነ ምድሩ ከቀኝ ጎኑ በአንጀቱ ይወጣል”።



EthioLion.Com

ሰሚ አጥተው በየቤቱ በጸጥታ የተዋጡ የሚጮህላቸው፤የሚዘግብላቸው የትግራይ ጋዜጠኛ ያጡ ዜጎች እሮሮአቸው ፍትሕ አጥቶ ለዓመታት የደም ዕምባ ያፈሰሱት የወያኔ ሰለባዎች የሆኑት የትግራይ ኗሪዎች፤ ቀሳውስትና ዲያቆናት በወቅቱ የትግራይ ክፍለሀገር (የትግራይ ክልል መንግሥት ይሉታል በዛሬው በወያኔዎች አጠራር) ገብሩ አስራት ፕረዚዳንት በነበረበት ወቅት “በረሃ እያለን ለፈጸምነው ወንጀል አንጠየቅበትም” ብሎ በወያኔ የተጠቁ ፍትሕ ፈላጊዎች በሥልጣን ማን ያህለኝነት ያሰናበታቸው አቶ ገብሩ አስራት እንደነበር በቲ ቪ በግልጽ መልሱ ተላልፎ እንደነበር ዲያቆን ብርሀነ ገብረህይወት ተናግሯል።

አስገደ ገብረስላሴ፤ ጋህዲ በተባለው መጽሐፉም ስለ አረጋሽ፤ቢተው በላይ፤ ሐሰን ሽፋ.....የተባሉ የወያኔ “አውራዎች” ለጦርነቱ ስልጣና እኛም ሆነ ልጆቻችን አንሰጥም፤አንመለመልም ላሉ ገበሬዎች፤“በተግራይ በሰፊው በተዘረጉ ማጎርያ ጣቢያወዎች ታስረው፤በብዙ ሺሕ የሚቆጠሩት በረሃብ እና በተስቦ በሽታ ሲሰቃዩ፤ የገብሩ አስራት ረዳት የነበረቺው ወ/ሮ አረጋሽ አዳነም የት እንደነበረች “አስገደ”በመጽሐፉ በሰፊው ገልጾታል”።

ድያቆን ብርሃነ ገብረህይወትም እንደዚሁ ወደ ሕዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ሕወሓት) ትግል ውስጥ እንዲቀላቀል የቀረበለትን ጥሪ ባለመቀበሉና በመቃወሙ፤ በተደጋጋሚ መታሰሩንና በመጨረሻም በአሰቃቂ ሁኔታ በሰባት ጥይት መደብደቡን ነግሮናል። ይህ ወጣት ቤተክርስቲያን በማገልገሉም ሳቢያ፤ ከፍተኛ ተጽዕኖ ተደርጎበት የዲቁና መታወቂያውንም የሕወሐት ታጋዮች ቀደውበታል። በተለይ ቢሆን የተባለው ታጋይ አንታገልም ካለችሁን ከትግራይ መሬት ወጡ! በማለት አፈር ከመሬት እያፈሰ በብርሃነ አፍንጫ ስር በማስጠጋት እንዲያሸተው ያደርግ እንደነበር ይገልጽል። ጋዜጠኛ ዮናስ “ዋርካ ስር” ተቀምጠው ቀና ፍትህ ይሰጡ ነበር፤ የሚላቸው የወያኔ ዳኞች ለነዚህ ግፉአን ምን ፍትሕ ይሰጡዋቸው እንደነበር ሊነግረን ይገባዋል።

እነኚህ የሚቀጣቸው፤ዳኛ ያልነበራቸው “ንጉሡ ነገሥታት የነበሩ አሁንም እየቀጠሉበት ያሉ የወያኔ ሽፍቶች” በሕዝቡ ላይ ምን ይፈጽሙ እንደነበር ብርሃነ ምን እንዳለ ባጭሩ አንዳንድ መረጃዎች ላስነብባችሁ።

“ወላጆቻችን ታሰሩ። የእርሻ ማሳዎቻችንም ተወረሰ። ቀንደኛ አድመኞች ናችሁ በተባልን በተወሰንን ሰዎች ላይ ከባድ ቅጣት ተፈጸሙብን። ከ6 ወር እስከ ዓመት በእስራትና በግርፋት ተቀጥተናል። ክንዶቹ ለረዥም ጊዜ በቀጭን ጅማት ነገር በመታሰራቸው ምክንያት ጣቶቹ ደም እስከ ማንጠባጠብ የደረሰ ጓደኛችንም ነበረ።እንዲህ የሆነው ጓደኛየ ሃለቃ ሓዲሽ የባላል። ቢዚያን ወቅት <ሙሽሮችና ካህናት> ሳይቀሩ <በህማማት ጊዜ ከቤተክርስቲያን> ተወስደው ከሽማግሌዎች በቀር ሁሉም ታፈሶ ተወሰደ። ለመሸሽ የሞከረውን እንደ ጅግራ

EthioLion.Com

እያሯሯጡ በጥይት ያሳድዱት ነበር። የካቲት ወር 1981 ጀምሮ ማለት ነው(ትግራይ ከደርግ ነፃ እንደወጣች ማለት ነው)።

ከዚያ... ሰው እንደ አውሬ በአካባቢው እየተበተነ በአካባቢው በቀን ሰው የሚባል አይታይም ነበር። እነሱም እንደ ጅግራ እያደኑ ይውላሉ፣ መሬታችንም ለታጋይ ቤተሰብ ታድሎ የምንቀምሰው የምንልሰው አልነበረም። ከቀበሌ ወደ ቀበሌ የሚያስተላልፉ የነሱ ካድሬዎች ካዩን ጥይት ይተኩሱብናል፣ የተኰሱብን ጥይት አልመታንም እንጂ ቁጥር የለውም። ከዚያ በኋላ እየተንከራተትንና እየተራብን ቆይተን ህዳር 21/1983 ዓ.ም. ገረዳ ተብሎ በሚጠራ ቀበሌ የገበሬ ማኅበር ለአቶ በርሄ እህል ስንሸከምላቸው ውለን፣.........” በማለት አሳዛኙ ታሪክ እና የወያኔ ታጋዮች የሽፍታነት ባህሪ ይዘረዝራል። ይቀጥል እና ብርሃነ እንዲህ ይላል፤

የክልሉ መንግሥት ጸሐፊት ወ/ሮ አረጋሽ አዳነን አነጋገርኳት።
ምን ሆንክ? አለችኝ።
በጥይት ተመትቼ
ማን መታህ?
የህወሃት ታጋዮች፤

እንዴ! ምን ብለው ይመቱኋል? ክሰሳቸው።

ምን ብየ እከሳቸዋለሁ? ታውቂት የለም እንዴ ራሳችሁ። እንደ ብርሃነ እንዳትሆኑ እያላችሁ መድረክ ላይ ስበሰባ ላይ ትናገሩ አልነበረም እንዴ? ከ500 ሕዝብ በላይ አቤቱታ ለማቅረብ ሲቀርብ በዱላ አላባበረራችሁትም? ወንጀለኛ ከሆንኩኝ ግደሉኝ፤ ካልሆንኩ ግን አሳክሙኝ። አናውቅም የምትሉኝ ከሆነ ደግሞ ስንብት ወረቀት ስጡኝና የትም ሀገር አቤት ልበል ስላት፡የለም ምንግሥት አይመታህም አለችኝ።

መንግሥቱ ኃይለማርያም አሰቃይቶ የገደለው ሰው የለም። የእርሱ ወታደሮች ግን ሰው ገድለዋል። የህወሐት ወታደሮችም እንደቅጠል ነው የቀጠፉን፤ የገረፉን። ዕድሜ ልካችንን ሲያሰቃዩን ነው የከረሙት። ስለዚህ ለውጥ የለውም። ፍርድ ቤት በደርግ ጊዜ ነበረ አሁንም አለ። ያለው ፍርድ ቤት (መንግሥታዊ) ነው እንጂ ማኅበራዊ (ነፃ) ፍርድ ቤት አይደለም። የመሰላችሁ ፍትሕ ስጡኝ። ስላት፡ “ግብረሰናይ ድርጅቶች ጠይቅ አለችኝ”። ከ300 በላይ ግብረሰናይ ድርጅቶችን አነጋግሬ "መንግሥት ማንንም ሰው በግለሰብ ደረጃ እንዳትረዱ የሚል ማስጠንቀቀያ ሰጥቶናል" ብለውኛል፡ እኔ ከ60 ሚልዮን ሕዝብ በላይ ስለማልበልጥ ብጠይቃቸውም መልስ አጥቻለሁ።ስላት “ይህንን ነገር እንዴት ልታወቅ ቻልክ?”አለቺኝ፡ይሄማ ግልጽ የሆነ እኮ ነው፤ ስላት “ይኼማ የፓለቲካ አዘማሚያ ነው” ብላ “ወዲ ሻምበል” የሚባለውን “የፖሊስ

አዛዥ" ጠራች ። አሱም መጣ። ሌሎችም ተከተሉ። ድምፅ እንኳ ወደማይሰማበት "አንደር-ግራውንድ" አስገቡኝ።

አንደርግራውንዱ አዚያው ምክር ቤት ውስጥ አካባቢ ነው ያለው?
ብርሃነ፡-
አዎ። ከ8፡00-1130 ድረስ ጎሮሮየ ደርቆ መናገር አስኪያቅተኝ ድረሰ በጥያቄ አፋጠጡቡኝ። የደረሰብህ ነገር ተንትነህ በሙሉ ንገረን፥ ያየኸው ነገር ሁሉ ተናገር፥ሙሉ መብት ሰጥተንሃል አሉኝ። እኔ በመጀመሪያ የቤተክህነት ተማሪ ነበርኩ። ወላጆቼ ቤተክርስቲያንን እንድታገለግል ለቤተክርስቲያን ሰጥተንሃል አሉኝ። እኔ በመጀመሪያ ደረጃ የቤተ ክህነት ተማሪ ነበርኩ። ዲቁናየ ስቀበል ደግሞ ታጋይ ሐጎስ የሚባል የወረዳ አስተዳዳር "የዲቁና የምስክር ወረቀቴን ቀደደው"። ቀጥለው ታገል ተባልኩ። እኔ አልታገልም ሰርቼ ነው የምበላው ስላቸው፡ "የለም መታገል አለብህ" አሉኝ። መጨረሻ "ወጣቱን በታኝ ነህ! አሳዳሚ ነህ!" አሉኝ። የበተንኩት ሰው የለም። ብርሃነ እንዳትታገል ብሎኛል የሚል ሰው ካለ አምጡት አልኳቸው። መጨረሻም ወጣቱን ማፈን ጀመሩ። እንደ አራዊት ማባረርና ማፈን ሲጀምሩን እኛም የምንገባበት ቦታ አጣን። ተረበሸን፤ የት እንሂድ? ገሚሶቹ ወጣቶች ወላጆቼ በእኔ ሰበብ ከሚሰቃዩ አኔ ልሙት እያለ ወደ ትግል ግምበር ሄዶ ሞቷል። እላዩ ላይ ሳር በቅሎበታል። የተቀረንም ሰውነታችን በጥይት ተበሳስቷል። እሳት ጨብጦ ፈንጅ ረግጦ ለሥልጣን ያደረሳችሁ ወጣት በየፈርማታው ወድቋል፡ ግማሶቻችንም ጠፍተናል።

ለምሳሌ ያህል
ይግዛው ጣሰው - ከማይጓጓ
ፍቱሕ ገ/ሕይወት - ከማይዳዕሮ
አለቃ ሐጎስ- ከማይደዕሮ
ገ/እግዚአብሔር-ከደዕሮ ሸዊቶ
ዓለምሰገድ ይግዛው-ከዳዕሮሸዊቶ
አረፋይኔ -ከገረዓ
አበበ ገብረአብ - ከገረዓ

ሲጠቀሱ ከነዚሁ አንዱ እኔ ነኝ።



ታፈነው ተወስደው የጠፉ፤ አድራሻቸው የጠፋ ናቸው። ስላቸው፥አሁንም የት እንዳሉ አይታወቅም? ብለው ጠየቁኝ። የሉም! በቃ!....ለአብነት ያህል ከነዚህ ሰዎች አንዱ እኔ ነኝ አልኳቸው። ጊዜ ከሰጣችሁኝ በመቶ ሚቆጠሩ ሰዎች አውቃለሁ አልኳቸው። በመጨረሻ መሬት ተወስዶብኛል ብለሃል ማን ነው የወሰደው? አሉኝ። እኔ እዚህ ሆኜ መሬቴ ተወስዷል፥መሬት የለኝም። የሚል መልስ፤ሰጠኋቸው።

በምን ትደዳራለህ አሉኝ፤ ለምኜ ዕድሜ ለሕዝቤ፤ የሚል መልስ ሰጠኋቸው። በል አሁን የምትፈልገው ምንድነው? ደረሰብኝ የምትለው በደልስ ምንድነው? አሉኝ "እኛ የትግራይ ተወላጆች በሦስት ፓርቲ ብዙ ችግር ደርሶብናል። ከኢትዮጵያ ሕዝብ በተለየ ሁኔታ የትግራይ ሕዝብ በደርግ በሻዕቢያ በሕወሓት ተበድሏል። እንደዚህ ሆኖ እያለ የደርግ ባለሥልጣኖች ለፈጸሙት ግፍ በፍረድ ቤት ሲጠየቁ እኛስ ለምን መፍትሔ ለምን አይሰጡንም? ለምሳሌ ለደርግ ባለሥልጣናት በጀት መድባችሁ ጠበቃ አቁማችሁ ፍ/ቤት እንዲቀርቡ አድርጋችኋል። በህወሐት እና በሻዕቢያ በኩል በደል የደረሰብን ሰዎችስ ምን እንሁን?እኛም እኮ ሰዎች ነን። ቅጠል አይደለንም። መፍትሔ ለምን አይሰጠንም? "ብየ መልስ ሰጠኋቸው። አንዲያውም የትግራይ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ገብሩ አስራት "በትግላችን ወቅት ያጋጠሙን አንዳንድ ችግሮች በአሁኑ ሰዓት ሊያስጠይቁን አይችሉም።" የሚል መልስ በመድረክ ላይ ተናገረ።

በስብሰባ ላይ የተናገረውና በቴሌቪዥን የቀረበ ነው ፤ መልስ የሰጠው። እኔ የተናገርኩት እና ሌሎችም ቤተሰቦቻችን አምጡልን፡ሞተውም እንደሆነ ንገሩን ብለው አቤቱታ በማቅረባቸው ነው። ከመርማሪዎቹ ከእነ ወዲ ሻምበል ጋር መጨረሻ ላይ አሁን የት ነው ምትኖረው አሉኝ? እኔም አቅጣጫ ቀይሬ እዚህ ቦታ ነው የምኖረው አልኳቸው። ተከትለው ሊይዙኝ ነው የፈለጉት። መቀሌ ውስጥ የሐሰት አድራሻ ነግሬያቸው ከከተማ ወጥቼ ቲኬት አስቆርጬ

EthioLion.Com

አ/አበባ መጣሁ። አ/አበባ እንደመጣሁ ድርጅቶች ውጭ ልከው አንዲያሳክሙኝ ጠየቅኩ።.......” ሲል ረገርም ታሩኩን እንዲያ እየዘረዘረ በመቀጠል ይናገራል።

ሌላው አንድ የማሳረጊያ መረጃ ልጥቀስለት እና ላሳርግ።

አቶ ገዛኢ ረዳ ይባላሉ። ወያኔዎች በእሳት ልብልበው አቃጥለው ተኝተው እንዳሉ በጥየት የገደሏቸው ከኔው አማች ጋር አብረው ታስረው የነበሩ ናቸው። እንዲህ ሲሉ የወያኔ ሽታዊ ባሕሪ በመጽሐፌ ውስጥ ይገልጻሉ። መርማሪያቸው የያኔው መርማሪ፤የዛሬው የወያኔ ጀኔራል እና የአገሪቱ አየር ሃይል ዋና አዛዥ የነበረው ብ/ጀኔተራል አበበ ተክለሃይማኖት (ጆቢ) ይባላል።

“.....የሰው ባሕሪ ርቋቸው ስለነበር የሰዉ ፍጡራን አልነበሩም።ሳንጃን እሳት ውስጥ አሙቀው ገላህን ይጠብሱሃል። የጓንዴ ሳንጃ በጣም ትልቅ ነዉ። ሳንጃዉ በሃይለኛ የእሳት ፍም ያኖሩ እና እሳቱን እያፋሙ ሳንጃዉ በከፍተኛ ግለት ያግሉታል። የጓንዴ ሳንጃ ነዉ። ሳንጃዉ እንደጋለ ወደ እሳትነት ተለዉጦ ብረቱ ቀይ ሆኖ ሲፍም የጋለው ሳንጃ ከእሳቱ ያነሱና የእስረኛዉን ገላ በጋለው ሳንጃ ይጠብሱታል።እያቃጠሉ፡ ደም በደም አስኪሆን ፤ዉሃ አስኪቋጥር ድረስ “አግዚኦ!!” እያለ ቢማጸንም ሰሚ የለዉም-ያቃጥሉታል።-ጭካኔዉ በጣም ብዙ ነዉ። በቃላት ለመግለጽ በጣም ያዳግታል። የነሱን ጭካኔ ለመረዳት በጭንቁ ውስጥ ካላለፉበት በቃላት ለመግለጽ በእወነቱ ይከብዳል።......”

...“ለምሳሌ ያለ ምንም ምክንያት ለምርመራ ብለው እኔን በእሳት ለማቃጠል ቀጭን እንጨት እና የሚቀጣጠል ሳር ዙርያየ ደርድረውበታል። ሊያቃጥለኝ የቆመው መርማሪየ ሰውየ እጁን ዘርግቶ በመለካት “አንድ ክንድ” ከለካ በኋላ እኔን ከዛፉ ጋር የፍጢኝ አስሮ ማገዶውን በዙርያየ ከምሮ የፍጥኝ እንደታሰርኩ ከዛፉ ዙርያ ኩምትር ብየ እንድቀመጥ አዘዘኝ። በአንድ ክንድ ርቀት በዙርያየ የተከመረው ሳር እና ቀጫጭን እንጨት በሳር አቀጣጥሎ እሳት ለኮሰበት። እንጨቱ መጀመሪያ ጭስ ማውጣት ጀመረ፤ ሳሩም መቀጣጠል ጀመረ ጭሱ አፈነኝ። ጭሱ ሲያፍነኝ ማስተንፈስ አልቻልኩም ጨነቀኝ። ጥልቅ ባሕር ውሃ ውስጥ ጠልቀህ ተውጠህ መዉጫ እናዳጣ ሰው ነው ትንፋሽ አጥሮኝ የተሰማኝ። ጭሱ በዙርያየ እንደ ጉም እየተልመለመለ ሲነሳ መርማሪየ ቆሞ አሳቱ ይበልጥ እንዲቀጣጠል ቆሞ ይቆጣጠራል ፤እኔኑም ያየኛል።

....ጭሱ ወደ እኔ እየገፋ እየበራታብኝ “አፈነኝ”። ሲያፍነኝ መሳል፤ማስተንፈስ አልቻልኩም። በጣሙን ጨነቀኝ። ነፋሱ በርትቶ ጭሱን ካስወገደው በኋላ፡- እንጨቱ እየተቀጣጠለ ወደ አሳት ተቀይሮ መንደድ ጀመረ። ነፋሱ ነበልባሉን በሁሉም አቅጣጫ ወደ እኔ ዙርያየ ይገፋው ስለነበር ገላየን መለበለብ ጀመረው። እጄ የፍጥኝ ታሰሬአለሁ። አግሬ እጄም መላወስ ስለማልችል፤ ወላፈኑ አሰቃየኝ። ሙቀቱ የቃጠለው ወላፈን ነብሰ ስጋየን አሰቃያት። ከጎን እና ከኋላ እየለበለበኝ



EthioLion.Com

ካለው ወላፈን ለመሸሽ እግሬን ወደ ፊት ለመዘርጋት ብሞክር ወደ ባሰ እሳት ይጠጋል። የማደርገው ጨነቀኝ። እጄ የፍጥኝ በጥብቅ ስለታሰረ፤ ያለሁት "ቁጭ" ብየ አግሮቼን "ኩምትር" አድርጌ ነውና ወደ ግራ ስል ወደ ቀኝ ወደ ኋሊት ማምለጫ የለኝም። ወደ ኋላየ እንዳላፈገፍግም ከዛፉ ጋር የፍጢኝ ተጣብቄ እንዳልንቀሳቀስ ታስሬአለሁ። ወዴት ልግባ!ወዲያዉኑ ሰዉነቴ ቆዳየ በመላ አካላቴ "ቱት.. ቱት.. ቱት.. ብሎ ዉሃ ከረጢት ቋጥሮ አበጠ።

መላ አካላቴ እሳቱ ስለለበለበኝ ሰዉነቴ ውሃ ቋጠረ። ወዲያውኑ እንደተሰበረ እንስራ "ቧ!!!!" ብሎ የቋጠረዉ ዉሃ ፈሰሰ! በኋላ፤ "ዕረፍት!" አሉኝ። አምላክ ዕረፍት አይስጣቸውና! ያሰሩኝን ፈቱልኝ። ሲፈቱኝ ወደ መሬት ተንጋለልሁ እና ተዘረጋሁ። ሰውነቴ ወደ መዛል ሲል "ተነስ!" አሉኝ። አእምሮየ የት እንዳለሁ አይታወቀኝም -ነገር ግን ትንሽ ትንሽ ይታወቀኛል። ተነስ ብሎ እንደገና ሳሩን በእሳት አቀጣጥሎ መሬት ላይ ተዘርግቼ እንዳለሁ "የተቀጣጠለው የሳር እሳት" እንደ ቀጤማ በላየ ላይ ወርውሮ በትኖ ፊቴን ለበለበኝ,,,,,,,,," እያሉ አሳዛኙ የወያኔ ሽፍታ ባሕሪ ከገለጹ በኋላ

በእውነቱ በወቅቱ ይህ ዓይነቱ ጭካኔ ሲደርስብን አንኳን ከትግራይ የተገኙ ወጣቶች ናቸው ለማለት ቀርቶ ሰው መሆናቸውም ተጠራጥረን "ከጋኔል ከሲኦል ወደ መሬት የሰው ልጅ ለመከራ እንዲዳርጉ የወረዱ አጋንንት ናቸው ነበር ያልናቸው። እንኳን እና የኛ ናቸው፤የእነ እገሌ ልጆች ናቸው ለማለት ቀርቶ በተአመር ወደ መሬት የወረዱ መናፍስት ነበር የምናስባቸዉ። እነሱን ስናይ እያንዳንዱ አስረኛ የሚያሳየዉ ጭንቀት ፍርሃት (ነብሰከ ታአምር ቀታሊሃ) ልክ አንደ ጋኔል ነበር የሚታዩን።

በማለት እንኳን እና ቀላሉ "ሽፍታ" የሚለው የወንብድና ባሕሪ መጠሪያ ቀርቶ፡ ከሲኦል የተላኩ ጋኔሎች" ነበር ተብለው በትግራይ አዛውንቶች የሚገለጹት። የተገለጹት ታሪኮችና ሌሎች መሰል ታሪኮች በሰፊው ለማንበብ መጽሐፍቶቼን አፈላልጎ ማንበብ ያስፈልጋል። ጽሑፉ ለፍትሕ ጋዜጣ ብልከው እንደማይታተም የተወቀ ስለሆነ እዚሁ ይተላለፍና መልሱን በድረገጽ እንዲያነቡት አስተላልፌአለሁ። ጌታቸው ረዳ (ኢትዮጵያን ሰማይ አዘጋጅ www.ethiopiansemay.blogspot.com አመሰግናለሁ። getachre@aol.com

EthioLion.Com